# «አይታ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሺ ቢኋት በየት ተመልሳ»

ከፀሐዬ ደባልቀው (ዋሽንግተን ዲ.ሲ.), ጃንዋሪ 25, 2012

ዛሬ ዛሬ በአናት ላይ ቁጢጥ ብለው እኛ እንመራሃለን፣ እናታግልሃለን፣ በማለት የሚፎክሩና የሚጮሁት የመብዛታቸው ፈሊጥ ፍንትው ብሎ የሚታየው የአንዳንድ የዳያስፖራው ሕብረተሰብ አባላት ለመበለጥና ለመበላት ዝግጁ መሆን ነው ቢባል እምብዛም፣ የተጋነነ አባባል አይሆንም:: ምነው ቢሉ አንድ ቀን በሚደሰኩሩትና በሚገቡት ቃል፣ እንዲሁም በሚደረድሩት ተስፋ የሚለኩ ከእነዚህ መካከል በአጋጣሚ እንኳን ዝር ሲሉ አለመስተዋሉ ነው::

ነገሩ ወዲህ ነው፣ አሁን አሁን እንደፋሽን የተወሰደውና እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ከልካይ ያጣ በሚመስለው ሂደት አንዳንድ ብልጣ ብልጦች የዳያስፖራው ሕብረተሰብ አባላት ማስነውና ላባቸውን አንጠ ፍጥፈው ያገኟትን ቤሳ ቤስቲን በአፈጮሌነትና በግርድፍ ወኔ ቀስቃሽነት ሲያራግፏቸው ሲታይ እረ ጉበዝ ምን ነክቶናል፣ የሚያስብል ክስተት ሆኗል::

የኛ ጉዶች! ያለንበት ሃገር የሥራና የኑሮ ብልሃት በቀላሉ የገባቸውና ብዙም ላብና ወዝ ሳያባክኑ ኪሳቸውን በግላጭ የሚሞሉበትና የወሬ ሱሳቸውን በቀላሉ እየተወጡ «የፖለቲካ አምሮታቸውን አለን አለን በማለት እየተኰፈሱ የሚዘባነኑበት መልካም አጋጣሚ የፈጠረላቸው ይመስላል::

አሁንስታ አንድ ወዳጄ «ዳያስፖራውን እኮ አራቆቱት እንታገልልሃለን የሚለትንም የፖለቲካ ዓላማ በ10ሺህ ማይልስ ላይ ተቀምጠው በምን ተአምር እንደሚያሳኩ ራሱ ግራ ይገባሃል ሲል አጫወተኝ»።

ታድያ ነገሩ ያለው በርቀት ሆነው ከእቶን-እሳቱ ርቀው ማቅራራቱና መሸለሉ ላይ አይደለም እንዴ የዚህ ዓይነቱ ትግል ትልቁ ፀጋ፣ ብዬ ስለው «እንደዚያ ባይሆንማ የዓላማም ድህነት ባይጠናወታቸው ኖሮ የሃገርንና የፖለቲካ ድርጅትን ጉዳይ እያምታቱ በሕዝብ የዘለቄታ ጥቅም ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉና እሳት እየለኰሱ የትውልድ ባላንጣነታቸውን ባደባባይ ባላረጋገጡ ነበር ብሎኝ አረፈው።»

እርግጥ ነው ባለንበት አገር እያንዳንዷ ሴኮንድ፣ ደቂቃ፣ ሰዓትና ቀን በልፋትና በውጤት ደረጃ የሚለካ፣ በኑሮ መስፈርት የሚመዘን ፋይዳና እንዲያም ሲል አንጡራ ሃብትን ከቻሉ መሰነቅ አሊያም የዕለት ተዕለት ተግዳሮቶችን ለመሻገር እየተጠቀሙ ኑሮን መግፋት ራሱ ፈታኝ ነው።

ታድያ የኛዎቹ ጮሌዎች በአቋራጭ ለመክበርም ይሁን ለመሰንበት ፖለቲካን አንግበው የፖለቲካ መዘውሩን ጨብጠው እረኸሙ ተሳቢ ላይ የሚሣፈረውን መንገደኛ የቆመበትንና የተቀመጠበትን ቦታ በዶላር እየቸበቸቡ መጓዝን የመረጡበት ስልት በቀላል አነጋገር የስብሰባ፣ የሬድዮና ለድራ-ገጽ፣ እንዲሁም የፓልቶክ አርበኝነት እደጉ ተመንደጉ በሚል ቅጽል

ታጅቦ የተንደላቀቀ ሕይወት እንዲኖሩ ስላስቻላቸው እንደሆነ አትጠራጠር ሲል ጥረቃውን ለጠቀ፣ እናላችሁ እኔም ቀጠልኩና ጌትነት ብቻውን ባልከፋ የሚገርመው ነገር እነኝህ ሳይለፉና ሳይታክቱ የተደላደለውን ኑሮ የሚቀጩት ጥቂት ዘመናውያን ይህ አልበቃ ብሏቸው ብዙሃኑ በዝንተዓለም ላሜ ቦራነት ጥገት ሆኖ እንዲታለብላቸው የሚጐነጉኑት ሴራ ነው በጣም የሚደንቀው አልኩት፡፡ ይኸውልህ እዚህ ምግብ ቤት ድርሽ ትይና በዚያ መነገድ ታልፍና፣ ከእገሌ ወይም እገሊት ጋር ታወሩና፣ እዚያ ቤተ ዕምነት ትገኙና፣ የታመመውን ወገናችሁን ትጠይቁና፣ ወዮላችሁ፣ እርኩስ ከመአርዮስ በማለት የፖለቲካ ውግዘትና እግድ ይጥሉባቸዋል፡፡ ይኸንን መሰሪ ተንኰል የሚሸርቡ ለምን ይመስልሃል በማለት ወዳጄ ሲተነትን «ሁሌም ምርኮኛ አለን፣ እኛ ግዳይ የፈፀምን ነን ባሉ ቁጥር የራሳቸውን ዋጋ ከፍ ከፍ በማድረግ ቆዳቸውን ያዋደዱ ስለሚመስላቸው ሲሆን ዋናውና አንኳር ሚስጢር ግን ሁሉም የነርሱን ደጀ ሰላም የሚሳለም ምዕመን አፋቸው ተለጉሞና ተሸብቦ፣ አእምሮአቸው ታፍኖና ዓይናቸው ታውሮ ሁሌም የነሱ ሲሳይ፣ ምቾትና ድሎት ተንከባካቢዎች ሆነው እንዲዘልቁ ለሀገርና ለወገን ደንታ የሌላቸው አሊያም ሃገራቸውንና ወገናቸውን በጥርጣሬ ዓይን እያማተሩ በጎውን ሳይሆን ክፉውን ሊመኙና ሊከውኑ የሚችሉ በሰው አምሳል የተፈጠሩ ግዑዛን ሆነው ዘለዓለም እየገበሩላቸው እንዲኖሩ ለማድረግ ባነጣጠረ ዒላማና ስሌት ይመስለኛል ካልኩት በኋላ በሃገራችን የቆየ ብሂል አገላለፅ እንደነዚህ ዓይነቱ ዘመናይና ቅንጡ ሰው፣ በሰው ላብ ከብሮ በሰው ጭንቅላት ላይ ወጥቶ እንደ ደም መጣጩ ትኋን ተመርጎ

መኖርንና መኮፈስን የተካነ ሰው «አይታ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሺ ቢሏት በየት ተመልሳ» እንዲሉ በማጭበርበርም በማስመሰልም በአጋጣሚ የጨበጠችውን ድሎት እንዳታጣ የሞት ሞቷን ትፍጨረጨራለች። ግና የዚች አይነቷ ግብዝ ፈሊጥ ብዙሃኑ ሲነቁባትና ሰብሰብ ብለው ፊታቸውን ወደራሳቸው፣ ወደወገናቸውና ወደ ሃገራቸው የመለሱ ዕለት እሷን አያድርገኝ፣ እራቁትዋን ቀርታ እውነትን ማየትና መጋፈጥ ስለማይቻላት ራሷን የምታጠፋበት አጋጣሚ ይፈጠራል በማለት ጨዋታዬን ቋጨሁ። በቸር ይግጠመን።